# የቀድሞው የኢትዮጵያ ጀግና ሰራዊት አኩሪ ታሪክ ወር መታሰቢያ ተመሰረተ።

አለም አቀፍ የእወቁልን መግለጫ፡ መስከረም 2010
ዳላስ ቴክሳስ ዩኒተድ ስቴትስ።

ይደረ ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ፡ ለተባበሩት መንግስታት እና ለአፍሪካ አንድነት ድርጅት።
"መስከረም የቀድሞው የኢትዮጵያ ጀግና ሰራዊት አኩሪ ታሪክ ወር"
ተብሎ ከዚህ አመት ጀምሮ በመላው አለም ኢትዮጵያውያን በሚገኙበት አገር ሁሉ መከበር ይጀምራል። እንደምታውቁት የኢትዮጵያ የቀድሞው ሰራዊታችን አለም አቀፍ ታሪክ ውስጥ የሚገኝ ባለ ትልቅ ታሪክ ባለቤት ነው። ይሄውም ከአፍሪካ ምድር ተነስቶ በኮሪያ ከሃያሉ ከአሜርካን ሰራዊት ጎን ተሰልፎ አንድም ወታደር በሙርከኝነት ሳይወድቅበት በጀግንነት ግዴታውን የተወጣ ነው። እናንተም ማለትም የተባበሩት መንግስታት ድርጅት እና የአፍሪካም አንድነት ድርጅት መዝግባችሁት የሚገኝ ነው። ነገር ግን የዚህ ግዙፍ የአፍሪካ ጀግና ሰራዊት ታሪክ ከእናት አገሩ ከኢትዮጵያ የታሪኳ መዝገብ ውስጥ እንዲወጣ ተደርጓል በጠላትነትም ተፈርጅዋል። በመሆኑም ለወጣቱ ትውልድ እና ለመጪው እራሱን የቻለ የኢትዮጵያ ታሪክ የሆነው የቀድሞውን ሰራዊት ታሪክ ከወደቀበት በማንስታት የሚገባውን ትልቅ ቦታ በኢትዮጵያ በአገሩ፡ በአፍሪካ አንድነት ድርጅት ፡ በተባበሩት መንግስታት ፡ በአሜሪካን መንግስት ፡ በአውሮፓ ሕብረት ጭምር እውቅና እንዲሰጠው የሁላችሁንም ትብብር እጠይቃለሁ።

የኢትዮጵያ ጦር ሀይል ጅምር ምስረታው ባጭሩ ለመግለጽ ፡ የተጠነሰሰው በአጼ ቴዎድሮስ ዘመነ መንግስት ቢሆንም ይህን ዘመናዊ ጦር አደራጅቶ የተፈለገውን አቅጣጫ ለማስያዝ ንገሱ የጋፋትን የጦር ኢንዱስትሪ በማቁዋቁዋም እርሾውን ቢያኖሩም በሀገር ውስጥ ተቀናቃኞቻቸውና በተለይም በባላንጣዎቻቸው ፊት መሪነት ከህንድ ሲገሰግስ በመጣው የናፒር ጦር የመዋከባቸው ነገር እቅዳቸውን ከግብ እንዳያደርሱ አድርጎዋቸዋል። ማይጨው ላይ በቀዳማዊ ኃይለስላሴ የሚመራው በጎበዝ አለቃ የተደራጀው ሕዝባዊ ጦር ከኢጣሊያ የጦር ኤርፕሌኖች በሚወረወር ኤፕሪት በተሰነው የኬሚካል ሙሌት ቦንብና መድፍ ተጠቅቶ ከተበተነ በሁዋላ ንጉሱ ለአቤቱታ ወደ ሊግ ኦፍ ኔሽን ሲያቀኑ በሀገሪቱ የቁርጥ ቀን ልጆች በሆለታ ገነት የጦር ትምህርት ቤት ሰልጣኝ መኮንኖች የተቁዋቁዋመው ኋላ ወለጋ ላይ ተደራጅቶ ራሱን የጥቁር አንበሳ ጦር ብሎ የሰየመው በኮሎኔል በላይ ኃይለአብ የሚመራው ጦር የፋሺስቱን የኢጣሊያ ጦር በመዋጋት ስንቅና ትጥቁን በመደምሰስ ከቦንያ እስከ ጎሬ ያካሄደው ፍልሚያ በታሪክ ፊት በአርአያነቱ ሁሌም ተጠቃሽ እና ለዘለዓለም የሚኖር የኢትዮጵያ ትልቁ የታሪኳ መዕራፍ መክፈቻ ሆኖ የጀግኖች ልጆቹዋ ታሪክ የሚመሰከርበት አንዱ የማይበረዝ ታሪክ ነው። ለዘመናት ሀውልቱ በሆለታ ገነት ጦር ትምህርት ቤት ጊቢ ውስጥ ተተክሎ የምናየው ጀግናው ኮሎኔል በላይ ኃይለአብ፣ ሻምበል ለማ አባይሬና ሌሎች የከፈሉት የህይወት መስዋእትነት ጅምር የኢትዮጵያ ጦር ሀይል ኩራት ሆኖ በታሪክ ተመዝግቦዋል ይሄውም ማንም ሊያጠፋው የማይችለው የኢትዮጵያ ታሪክ የሆነው በቀድሞው የኢትዮጵያ ሰራዊት ደም እና አጥንት የተተከለ የማይደርቅ እና የማይነቀል በታሪክ ሕይወት ውስጥ የሚኖር ቋሚ የኢትዮጵያ ታሪክ ነው።

የኢጣሊያ ጦር በጀግኖቹ የኢትዮጵያ አርበኞች ተጋድሎ ድል ተደርጎ በተባረረ ማግስት 1934 መካከለኛ ወራት ላይ በራስ አበበ አረጋይ ሚኒስትርነት በጄኔራል አብይ አበበ ኤታ ማጆር ሹምነት በሀያ ሶስት እግረኛ ሻለቆች የጦር ሚኒስቴር ተቋቋመ ። ይህ ሙሉ ወታደራዊ ኃይልም ከዚህ ጊዜ በኃላ የሀገሪቱን ዳር ድንበርና ሉአላዊነት ለማስከበር በሰንደቅ አላማዋ ስም ማለ በዚህም መሰረት በዳኖት በቶጎ ውጫሌና በሌሎችም የምስራቅ ኦጋዴን በረሀ ውጊያዎች ያስመዘገበው ድል የጀግንነቱ ምሳሌ ነበር። በ1943ዓ.ም በተባበሩት መንግስታት ትእዛዝ በኮሪያ ልሳነ ምድር የደፈረሰውን ጸጥታ ለማስከበር ወደ ኮሪያ የዘመተው በሜጀር ጄኔራል ተሾመ እርገቱ የሚመራው የኢትዮጵያ ጦር በውጊያው አንድም ምርኮኛ ሳይኖረው የውጊያ ጊዜውን ያጠናቀቀና በአሜሪካው የወቅቱ ፕሬዚዳንት ጄኔራል ሀይዘነሀወርና የተባበሩት መንግስታት ዋና ጸሀፊ ዳግ ሀመር ሾልድ ከፍተኛ ዝናና ሽልማት የተቸረው ነበር። በ1962 ዳግም በተባበሩት መንግስታት የጸጥታው ምክር ቤት ውሳኔ መሰረት በሜጀር ጄኔራል ከበደ ገብሬ አዛዥነት ኮንጎ ዘምቶ አኩሪ ገድል ያስመዘገበው የኢትዮጵያ ጦር የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ጸሀፊን የ ዩ ታንትን ከበሬታና አድናቆት አግኝቶዋል።

የ1966ዓ.ም አብዮት በኢትዮጵያ ከመጣ ወዲህ የአጼ ኃይለስላሴ ፡ ማለትም የንጉሰ ነገስቱ መንግስታዊ ስርዓት ቢቀየርም ያ ጀግና ጦር በተደራጀ መልክ ተዋቅሮና ተጠናክሮ ወታደራዊ ግዳጁን ማለትም የአገሩን ዳር ድንበር ማስከበር ቀጥሎዋል ። ሀረርጌን ከኢትዮጵያ ነጥሎ የራሱ ግዛት ለማድረግ ከንቱ ህልም የነበረውን የዚያድ ባሬን ጦር ለመደምሰስ የተከፈለው መስዋእትነት ቃላት የሚገልጸው አይደለም ። ያ የጠላት ጦር በዘመናዊ መሳሪያ የተደራጀ ከፍተኛ ወታደራዊ ብቃት የነበረው ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያ ጦር አይቶትም ሰምቶትም የማያውቀውን የጦር መሳሪያ የታጠቀ ነበር ይሁን እንጂ ከመሳሪያ በላይ በታጠቀው ሀገራዊ ወኔ ውጊያ የገጠመው የኢትዮጵያ ጦር በብዙ የደምና አጥንት ግብር የዚያድ ባሬን ህልምድምጥማጡን

አጥፍቶ ወደ ቅዥት ለውጦታል ። ጀግኖቹ የኢትዮጵያ ጦር ሀይል አባላት ገድል በአንድ አቅጣጫ ብቻ ሳይሆን ጠላት ያስታጠቃችፈው የጠላትን ማስከ ያጠለቁትን በሰሜን ኢትዮጵያ በብዙ ማእዘን የሚዋጉበት ጊዜም ነበር። ማለትም እንደሚታወስው በሰሜን ኤርትራን እና ትግራይን ለመገንጠል ያሰፈሰፉትን ሀይላት ለ17 አመታት ያለመሰልቸት በመዋጋት የሰራዊቱ አባላት የከፈሉት መስዋእትነት በታሪክ ፊት ግዙፍ እራሱን የቻለ አንዱ የኢትዮጵያ ታሪክ አካል ነው። በሳህል፣ አልጌና፣ ከረን፣እቆርዳት፣ ጋሎጅ፣ ከርከበት፣ ምጽዋ፣ ባሬንቱ፣ ኢላበረድ፣ በትግራይ መሬቶች እና በሌሎች አውደ ውጊያዎች የበላይነት ይዘውና ወንበዴን መግቢያ መውጫ አሳጥተው የነበሩት ጀግኖች በመንግስትና በጥቂት መኮንኖች የአመራር ድክመትና በዓለም አቀፍ የፓለቲካ መወሳሰብ ምክንያት ያን በደም የገነቡትን ድል ተነጠቁ ። የኤርትራ ሕዝብ ነጻ አውጪ ግንባር እና የትግርያን ሕዝብ ነጻ አውጪ ግንባር ማለትም አንዱ የኤርትራ ሕዝብ ነጻ አውጪ ግንባር ቅርንጫፍ የአነውም በውጊያ ያጡትን ድል በአረብ ሀገራትና ኮሚኒስቱን የኮሎኔል መንግስቱን መንግስት አምርረው በሚጠሉ ኃይላት አጋዥነት ያለውጊያ ተሩዋሩጠው የአራት ኪሎን ቤተመንግስት በመያዝ ያን ዝና ብዙ አይበገሬ ጦር በተኑት። በነዚያ ውጊያዎች ፍጹም ወደር የማይገኝለት መስዋእትነት የከፈሉ የጦር መሪዎችና ወታደሮች ውድ ሕይወታቸውን በክብር ሰጥተዋል ጥቂቶቹን ለመጥቀስ ፡ እነ ኮሎኔል ካሳ ገብረማርያም ፡ ጀኔራል ሃዲስ አግላቸው ፡ ጀኔራል በረታ ጎመራው፡ ብርጋዲየር ጀኔራል ተሾመ ተሰማ እንደ አጤ ቴዎድሮስ ጥይታቸውን ጠጥተው በታገሉባት ዳርድንበራቸው በቀይ ባሕር በምጽዋ ባሕር እራሳቸውን የአሰነባሪ እራት ያደረጉት ዘለግላጋ የኢትዮጵያ ጀግና፣ ኮሞዶር በለገ በለጠ፣ ኮሎኔል ተመስገን ገመቹና ሌሎች በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ከጀኔራል መኮንን እስከ ሰፊው መለዮ ለባሽ ወታደር ድረስ ያሉት የጦር ኃይል አባላቶቻችን ዛሬ የምንዘክራቸውና አንድ ቀን ታላቁን ሃውልት የምናቆምላቸው ለአንዲት ኢትዮጵያ መስዋእትነት የከፈሉ ጀግኖች ናቸው። ያጀግና ሰራዊት ፡ ከሁሉም ኢትዮጵያዊ አብራክ የወጣው ለኢትዮጵያ ያለምንም የብሄር ልዩነት እና የግል ጥቅም በገንዝብ ላይ ያልተመሰረተ ፡ ነገር ግን ኢትዮጵያን እና ክብሯን ልአላዊነትዋን ብቻ በማስቀደም "ልሙትላት ለውዷቱ ሃገሬ ወቶ አደር ነኝ"ብሎ በመነሳት ያለውን ሃብቱን ሕይወቱን ለኢትዮጵያ ክብር ሲል ገብርዋል። በነብስም ያለው ያደረገው ተጋድሎ ሕይወቱን ከሰጠው ያላነሰ ነው። ይሄ አቻ የማይገኝለት ብቸኛው አፍሪካዊ ሰራዊት ትልቁ የኢትዮጵያ እና የመላው አፍሪካ ታሪክ ያስመሰከረ በኮንጎ በኮሪያ ጭምር በመሆኖ በኢትዮጵያ በተወለደበት እና ባደገበት ምድር ብቻ ሳይሆን በመላው አፍሪካ አሃጉር ክብሩ በሚገባ ተተክሎ ሊኖር ይገባል ይደረጋልም። በኮሮያ ሃውልቱ ስሙ እንደተቀመጠው በአሜሪካንም ይተከላል በማንም ሳይሆን በራሱ በተባበሩት መንግስታት እና አሜሪካን አማካኝነት።

እነዚህን ጀግኖች በዚህ ወር ስንዘክራቸው ልንገነዘበው የሚገባን ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻ የጦሩ የግብረኃይል፣ የክፍለጦር፣ የብርጌድ፣ የሻለቃ፣ የሻምበልና የመቶ አደረጃጀት በዘር ያልተቡዋደነ መሆኑ ነው ። በመሆኑም የጦሩ ለአንዲት ኢትዮጵያ ፡ ለአንዲት ሰንደቅ ዓላማ የመቆም ጽናቱ ሁሌም በልባችን ውስጥ እየበራ እንዲኖር አድርጎታል። ይሄውም ትልቁ ግዙፉ የኢትዮጵያ ታሪክ በመሆኑ እንደዋዛ በዝምታ ቢታለፍ ኢትዮጵያን ግማሽ ማንነትዋን ጀግንነትዋን አዲሱ እና የሚቀጥለው ትውልድ እንዳያውቅ እና አንገቱን ቀና አድርጎ እንዳይሄድ ያደርገውል የእንዳይሆን ጊዜው መጥቶ ትልቁ የሰራዊቱ የጀግንነት ከተማ ከእነ ሃውልቱ እስኪገነባ ድረስ ፡ በእያአመቱ "መስከረም የቀድሞው የኢትዮጵያ ጀግና ሰራዊታችን አኩሪ ታሪክ ወር" በሚል ታሪኩ እየተዘከረ በአለም አቀፍ ደረጃ በእያመቱ ይቀጥላል።

ከትልቅ አክብሮት ጋር፡

ክብር ለዛ ገናና ታሪክ ላለው የኢትዮጵያ ጦር ሀይል!!!

የኢትዮጵያወርቅ (የሐረርወርቅ)ጋሻው  መስራች።